## ማወቅ ያለብዎት የሕግ ቃላቶች፡-

- ክስ ማቅረብ /arraignment/፡- የክስ ዝርዝር በስርዓት የሚሰማበት እና ተከሳሽ የሚለይበት፣ እንደዚሁም ተከሳሽ የተነበበውን ክስ በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ቃል የሚሰጥበት ሒደት
- ማስያዣ /bond/፡-ተከሳሽ በተከሰሰበት ክስ ከእስር ቤት ለመውጣት መክፈል ያለበት የገንዘብ መጠን
- የችሎት መራዘም /continuance/፡- የፍርድ ቤት ችሎት ለሌላ ቀን መተላለፍ
- ተከሳሽ /defendant/፡-ክስ የተመሰረተበት ግለሰብ
- የክስ መሰማት /hearing/፡-የፍርድ ቤቱ ዳኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉን መረጃዎች የሚሰሙበት ሒደት
- ከሳሽ /Plaintiff/ ፡-በፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብ እና የሚመሰርት ወገን፤ በወንጀል ጉዳይ ክስን በተከሳሽ ላይ የሚያቀርበው መንግሥት (አቃቤ ሕግ) ይሆናል
- ቅድመ ችሎት /Pre-trial/ ፡-አቃቤ ሕጉ እና የመከላከያ ጠበቃው በክሱ እውነታዎች ላይ ለመወያየት የሚሰበሰቡበት ቀን
- አቃቤ ሕግ /prosecutor/፡-መንግስትን ወግኖ በተከሳሽ ላይ የወንጀል ክስ የሚመሰርት የመንግስት ጠበቃ
- የቅጣት ፍርድ መስጠት /sentencing/፡-ዳኛው ወይም ጁሪው በተከሳሹ ላይ የቅጣት ብይን የሚወስኑበት ሒደት
- መጥሪያ ትዕዛዝ /subpeona/፡- አንድ ምስክር ከፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያዝ ሕጋዊ ሰነድ
- ምስክርነት /testimony/፡-አንድ ምስክር በፍርድ ቤት መሐላ ፈጽሞ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል
- (የፍርድ) ችሎት /trial/፡- ማስረጃ እና የምስክርነት ቃል ከቀረበና ከተሰማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት የፍርድ ሒደት



ስለ ደህንነት እቅድ፣የማህበረሰብ ሀብቶች ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት መርሐግብሮች እና አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የአቅራቢያዎን የቤት ውስጥ ጥቃት ፕሮግራም ያነጋግሩ።

Ohio Domestic Violence Network ODVN

የኦሀዮ የቤት ውስጥ ጥቃት አውታረመረብ / network/
800-934-9840 ወይም 614-781-9651
www.odvn.org

ስለ ነፃ የሕግ ድጋፍ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የኦሃዮ የሕግ አገልግሎቶችን ያነጋግሩ፡-
866-529-6446
www.ohiolegalhelp.org

Ohio Domestic Violence Network ODVN

The Ohio Domestic Violence Network (ODVN is a statewide coalition of domestic violence programs, supportive agencies, and concerned individuals working together to stop domestic violence through education, information and training for those who are affected by domestic violence, and by promoting social and systems change.

This project is supported by Grant No. G-1901OHSDVC awarded by the Department of Health & Human Services, Administration for Children and Families (ACF), Administration on Children, Youth, and Families (ACYF), Family and Youth Services Bureau (FYSB). The opinions, findings, conclusions, and recommendations expressed in this publication, program, exhibition are those of the author and do not necessarily reflect the views of the Department of Health & Human Services.



AMHARIC CRIMINAL COURTS BROCHURE

# የቤት ውስጥ ጥቃት ወንጀል ነው።



Ohio Domestic Violence Network ODVN

የቤት ውስጥ ጥቃት በተደጋጋሚ በኃይል/በማስገደድ የሚፈጸም ጥቃት ነው። በኦሀዮ ውስጥ አንዳንድ የቤት ውስጥ ጥቃት አይነቶች በወንጀል የሚፈረጁ ናቸው። በመሆኑም ለሕግ አስከባሪዎች በመደወል ወይም በአካባቢዎ ካለው የአቃቤ ሕግ ቢሮ በመሄድ ወንጀሉን ማመልከት/ማሳወቅ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ ጥቃት ከሚያደርስብዎት ሰው ጋር ያሎትን ግንኙነት ለማቆም ወይም ለመለያየት ወስነው እርምጃዎችን ለመውሰድ ሲያስቡ አደጋ የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ይጨምራሉ። የሚወስዷቸው የሕግ አማራጮች የተወሰነ ከለላ እና ጥበቃ ሊሰጡዎት ይችላሉ። ነገር ግን ለደህንነትዎ ፍጹም ዋስትና አይሰጡም።

በሲቪል ወይም በወንጀል ጉዳዮች የሕግ አማራጮችን ቢወስዱም ግላዊ የደህንነት ዕቅድ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው። ስለ ደህንነት እቅድ የበለጠ ለማወቅ የአከባቢዎን የቤት ውስጥ ጥቃት መርሃግብር ያነጋግሩ።

## የአነስተኛ ወንጀል መደበኛ አሰራር

የሚከተለው የአሰራር ሒደት የተለመደ ቢሆንም፤ የእርስዎ ጉዳይ ልዩ ሊሆን እንደሚችል ያስተውሉ። በአንድ የተወሰነ የወንጀል ጉዳይ ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የአካባቢውን የወንጀል ተሟጋች ወይም አቃቤ ሕግ ቢሮን ያነጋግሩ።

1. አንድ የተፈጸመ ወንጀል በተጠቂው ፣በምስክር ፣ ወይም በሕግ አስከባሪ ሪፖርት ይደረጋል።
2. ሕግ አስከባሪው ወይም አቃቤ ሕጉ ክስ ለመመስረት በቂ ማስረጃ መኖሩን ይወስናሉ።
3. ተጠርጣሪው / ተከሳሽ በቁጥጥር ስር እንዲውል ይደረጋል ወይም ከፍርድ ቤት እንዲቀርብ የመጥሪያ ትእዛዝ ይሰጠዋል። ይህም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እና ወቅት ወይም በኋላ ሊከናወን ይችላል።
4. ተከሳሽ በመደበኛ የክስ ማቅረብ /arraignment/ ሂደት (ወይም አንዳንድ ጊዜ ከመደበኛው አሰራር በፊት) ክሱን እንዲሰማ ይደረጋል፣ ጠበቃ እንዲያገኝ ሊጠይቅ ይችላል፣ የእምነት ክህደት ቃሉን ይሰጣል፣ የማስያዣ /bond/ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል። እንደዚሁም ተጎጂው ጊዜያዊ የጥበቃ ትእዛዝ (TPO) ሊጠይቅ ይችላል። ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ/አቤቱታ ከካደ/ካልተቀበለ፣ጉዳዩ ይተላለፍና ሌላ የቅድመ ችሎት ቀጥሮ ይያዛል።
   - ሀ/ አንዳንድ ጊዜ ተከሳሽ ከክስ መሰማት ሒደት ውጪ ወይም የክስ መሰማት ቀጠሮ ከመያዙ በፊት ማስያዣ በመክፈል ይለቀቃል። ይህ ማለት ተከሳሹ ከመለቀቁ በፊት ጊዜያዊ የጥበቃ ትእዛዝ (TPO) ለመጠየቅ እድል ላያገኙ ይችላሉ ማለት ነው። አስቸኳይ የደህንነት ስጋት ካለብዎ ግን ወዲያውኑ የአካባቢውን ተሟጋች ወይም ጠበቃዎን ያነጋግሩ። የደህንነትዎ ጉዳይ በመደበኛ የክስ ማቅረብ ሒደት ውስጥ እስኪታይ መጠበቅ የለብዎትም።
5. ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለሁም ካለ፣ የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብ እና / ወይም በቅድመ ችሎት /pre-trial/ ጊዜ ወይም ከፍርድ ችሎቱ /trial/ ማንኛውም ጊዜ በፊት በእምነት ክህድት ቃሉ ላይ ከስምምነት ሊደረስ ይችላል። ተከሳሽ ጥፋተኛ ነኝ ካለ ወይም ክሱን ካልተቃወመ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ወዲያውኑ ወደ የቅጣት ፍርድ /sentencing/ መስጠት ሒደት ለመሄድ ይችላል።
6. በእምነት ክህድት ቃሉ ላይ ከስምምነት ካልተደረሰ፤ የፍርድ ችሎቱ ተከሳሹ የፈጣን ችሎት መብቱን ካልተወ በስተቀር በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ይካሄዳል።
7. ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ወይም ጥፋተኛ አለመሆኑን ዳኛው ወይም ጁሪው ግልጽ ያደርጋል።
8. ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ዳኛው የቅጣት ብይኑን ያሰጣል ወይም የቅጣት ፍርዱ የሚተላለፍበትን ቀነቀጠሮ ያሳውቃሉ። ዳኛው የቅጣት ፍርዱን ከመውሰናችው በፊት ተጎጂው /ከሳሽ/ ወንጀሉ በህይወቱ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደረ የመግለፅ እና የመናገር መብት አለው።
9. የቅጣት ፍርዱ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡- የእስር ጊዜ፣ የማህበረሰብ ቁጥጥር /community control/፣ የጠፋን (ገንዘብ፣ንብረት) መመለስ/መተካት እና / ወይም የቅጣት ክፍያ። የማኅበረሰብ ቁጥጥር የአመክሮ ትእዛዝ ሲሆን ይሄውም (በተቆጣጣሪ መኮንን ወይም በኮምፒተር መቆጣጠሪያ አማካይነት) ተከሳሽ በዳኛው የተላለፉትን ሕጎች ማክበሩን እና መከተሉን የሚያረጋግጥ ነው። የአመክሮ ትእዛዝ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡- ከተወሰነ ቦታ ወይም ሰው መራቅ፣ ሕግን አለመጣስ ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ግዴታን መወጣት/ማጠናቀቅ ፣ ወደ ምክር አገልግሎት መሄድ ፣ ከአልኮል ወይም የአደንዛዥ ዕፅ ጋር የተያያዘ ሕክምናን ማጠናቀቅ ፣ ጥቃት ፈጻሚን /batterer/ ለማረም የሚዘጋጅ አጋዥ ትምህርትን መከታተል ፣ እንደዚሁም ካሳ መክፈል (ከወንጀሉ ጋር ለተዛመዱ ወጭዎች ለተጎጂው የሚከፈል)።
   - ሀ/ እነዚህ የሕግ ውጤቶች ደህንነትዎን በማስጠበቅ ረገድ ሊረድዎትም ላይረዱዎትም ይችላሉ። ስለ ደህንነትዎ እና የክሱ ሁኔታ ላይ በእርስዎ ላይ ስላደረሰው ተጽዕኖ ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን ተሟጋች ያነጋግሩ።

ለቤት ውስጥ ጥቃት ወንጀል ሕጉ የሚከተለው አካሄድ የተለየ ነው። ተከሳሽ የቤት ውስጥ ጥቃት ጥፋተኛ ሆኖ የተከሰሰ ከሆነ፣ ሰለሚወሰዱት እርምጃዎች የበለጠ ለማወቅ ተሟጋችን ወይም የአከባቢውን አቃቤ ሕግ ያነጋግሩ።

## ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ (TPO) ምንድነው?

አንድ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ እና፣ ወንጀሉ በፍርድ ቤት እየታየ ባለበት በማንኛውም ወቅት ተጎጂው ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ (TPO) እንዲሰጠው ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ ይችላል።

ይህ ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ የወንጀል ክሱ በፍርድ ቤት እስኪዘጋ ድረስ የሚያገለግል /የሚጸና/ ሲሆን ተከሳሽን የሚከተሉትን ድርጊቶች እንዳይፈጽም የሚያግድ ትእዛዝ ነው።

- ተጎጂውን በስልክ ፣ በደብዳቤ ፣ በኢሜይል ወይም በሌላ ሰው በኩል ማነጋገር፣
- በየትኛውም ስፍራ ቢሆን ከተጠቂው መቅረብ፣
- በመኖሪያ ቤት ውስጥ ከተጎጂው ጋር ተጋርቶ መኖር፣
- የመኖሪያ ቤት አስፈላጊ መገልገያዎችን /ጋዝ፣ኤሌክትሪክ ... ወዘተ/ ማዘጋት

ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ አንዳንድ ጊዜ የልጆችንም ጉዳይ ሊያካትት ይችላል። ብዙውን ጊዜ ይህ ትእዛዝ እንዲሰጥ የሚጠየቀው በክስ የማቅረብ ስርዓት /arraignment/ ወቅት ሲሆን፣ ነገር ግን ተከሳሽ ታስሮ ከነበረ ከእስር ከመፈታቱ በፊት የመከላከያ ትእዛዝ የመጠየቅ እድል ላያገኙ ይችላል።

በተጨማሪም የጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዙ አገልግሎት የወንጀል ክሱ በፍርድ ቤት ሲዘጋ /ክሱ በሚቋረጥበት ጊዜ/ አብሮ የሚያበቃ መሆኑን፤ ይህም በየትኛውም የችሎት ቀን ወይም በተለያዩ የችሎት ቀናት መካከል በድንገት ሳያውቁት ሊሆን እንደሚችል ማስታወሱ ጠቃሚ ነው።

ጊዜያዊ መከላከያ ትእዛዝን መተላለፍ/መጣስ ወንጀል ነው። ተከሳሽ ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝን ከጣሰ ወዲያውኑ ለሕግ አስከባሪ አካላት ወይም ለአከባቢዎ አቃቤ ሕግ ቢሮ ይደውለው ያሳውቁ። ደህንነትዎንም በተመለከተ በተሻሉ አማራጮች ላይ ለመወያየት የአካባቢዎ ተሟጋችን ወይም ጠበቃን ፈጥነው ያነጋግሩ።

## መብቶችዎን ይወቁ!

እንደ ተጠቂ ፣ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-

- ግላዊነትን እና ደህንነትዎን በሚጠብቅ አክብሮት እና ፍትሃዊነት የመስተናገድ፣
- በሚጠይቁት መሰረት የሁሉንም ችሎትና፣ የሕግ አካሄድ ላይ መረጃ የማግኘት እና በዛም ላይ የመገኘት፣
- በአብዛኛዎቹ ችሎቶች በክሱ ጉዳይ ላይ የመደመጥ፣
- ከተከሳሽ ወይም ተከሳሽን ከሚወክል ማንኛውም ሰው የሚከላከል ተመጣጣኝ ጥበቃ የማግኘት፣
- በሚጠይቁት መሰረት ተከሳሽ ከእስር ሲፈታ ወይም አምልጦ ሲገኝ መረጃ የማግኘት፣
- በተከሳሽም ሆነ በተከሳሽ ተወካይ የሚቀርብ ቃል የመስጠት / መረጃ የማግኘት ጥያቄን ወይም ቃለ መጠይቅን ያለመቀበል
- (ለደረሰብዎት የኢኮኖሚ ኪሳራ ማካካሻ) ከተከሳሽ የገንዘብ ካሳ የማግኘት፣
- ያልተጓተቱ የችሎት እና የሕግ ሒደቶችን የማግኘት እና ውጤቶችንም ሳይዘገዩ የማወቅ፣
- በሚጠይቁት መሰረት ፣ ከአቃቤ ሕጉ ጋር የመነጋገር ፣እንደዚሁም
- ሁሉንም መብቶችዎን የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ የማግኘት
- በእያንዳንዱ ችሎት እና የፍርድ ሂደት ላይ ከተጎጂ ተሟጋች ጋር የመቅረብ፣
- በዚህ ጉዳይ፣ ጊዜያዊ የመከላከያ ትእዛዝ (TPO) የመጠየቅ፣
- ምስክርነት እንዳይሰጡ የሚያስጠነቅቅዎ እና የሚስፈራራዎ ሰው ቢኖር ያለመደንገጥ እና ያለመፍራት፣ በዳይ ፣ የበዳይ ጠበቃ ወይም ሌላ ሰው በማስፈራራት ከሕጉ ጋር እንዳይተባበሩ የሚያደርግ ነገር ቢናገሩ ወይም ቢያደርጉ ወዲያውኑ ለተሟጋችዎ እና ለአቃቤ ሕጉ ያሳውቁ።

ከነዚህ መብቶች ውስጥ የተወሰኑት እርስዎ ጠይቀው የሚያገኙዋቸው ናቸው። መብቶችዎን በፅሁፍ ለመጠየቅ በ www.ocvjc.org/marsys-law ይግቡና መጠየቂያ ቅጹን ያግኙ።

Ohio Domestic Violence Network
ODVN

odvn.org | 800-934-9840